# መጪው ዘመን በእርግጥም የከፍታ እንዲሆን …

## ኢዛና ዘመንፈስ

09-08-17

ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም የተለየች ጥንታዊት ሀገር የሚያሰኟዋት በርካታ ታሪካዊ፤ ባህላዊና መንፈሳዊ ይዘት የተላበሱ ቅርሶች (ትውፊቶች) ስለመኖራቸው ተደጋግሞ የሚወሳ ጉዳይ ነው። በተለይም የራሷ የሆነ የዘመን አቆጣጠር ቀመር የምትከተልና ይህንኑ የጊዜ መቁጠሪያ ስሌቷን ለሺህ ዓመታት ያህል ተግባራዊ ማድረግ የቻለችም ጭምር ስለመሆኗ አያሌ የዓለማችን የታሪክ ድርሳናት ላይ ተመዝግቦ ይገኛል። ምንም እንኳን እኛ የድህረ ዘመነ መሳፍንቷ ኢትዮጵያ ትውልዶች ከወረስነው ስር የሰደደ ድህነትና ኋላ ቀርነት የተነሳ፤ የጥንታዊ ማንነታችን መገለጫ ተደርገው ስለሚወሰዱት ሀገራዊ የጋራ ወይም ደግሞ የተናጠል ትውፊቶቻችን ይዘት በቂ የሚባል የጥናትና ምርምር ስራ አለመስራታችን ቢታመንም፤ ኢትዮጵያችን በእርግጥም "ምድረ ቀደምት" የመሆኗ ጉዳይ ግን የሚያከራክር አይደለም።

እናም እንደመታደል ሆኖ በኢትዮጵያውያን የዘመን ቀመር መሰረት፤ ሁለተኛው ሺህኛ ዓ.ም አልፎ ወደ ሶስተኛው ሺህኛ ዘመን የተሸጋገርንበትን የ"ሚሌኒየም" በዓል ለማክበር የበቃነው የዛሬ አስር ዓመት እንደነበር አይዘነጋም። ያን ኢትዮጵያውያን ህዝቦች እንደ ህብረተሰብ በከፍተኛ ድምቀት ያከበርነውን የሚሌኒየም በዓል ስናስታውስ አብሮ መነሳት የሚኖርበት መሰረታዊ ጉዳይም ደግሞ፤ የኢፌድሪ መንግስት ታሪካዊ አጋጣሚውን እንደመልካም ዕድል በመጠቀም፤ ሀገራችንን ወደቀደመ የዕድገትና ስልጣኔ ከፍታዋ ለመመለስ የሚያስችለንን አጠቃላይ መነቃቃት ለመፍጠር ሲል ያሳየው ብርቱ ጥረት ይሆናል። ያ በኢፌድሪ መንግስት ያላሰለሰ ጥረት ምክንያት የታቀደና የተተገበረ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ክብረ በዓል፤ ሀገራችን የጥንታዊ ታሪክ ባለቤት ስለመሆኗ ለማያውቁ የሌላው ዓለም ማህበረሰቦች የማይናቅ አዎንታዊ ግንዛቤ ያስጨበጥንበት ነበር ተብሎ ከመታመኑም ባሻገር፤ አሁን ላይ የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ እያልን የምንጠራውን ፈርጀ ብዙ የልማት ንቅናቄ ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋገረ የፀረ ድህነት መንፈስ አስርፆብን ማለፉም የሚካድ ጉዳይ አይሆንም።

ከዚህ የተነሳም ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድ ወቅት የገናና ስልጣኔ መገለጫ ተደርገው ይቆጠሩ ከነበሩ ጥቂት የዓለማችን ጥንታዊ ሀገራት መካከል አንዷ እንደነበረችና አሁንም ወደ ቀደመ ታሪካዊ ከፍታዋ ለመመለስ በሚያስችላት ትክክለኛ የስር ነቀል ለውጥ ጎዳና ላይ እንደምትገኝ የሚያትት ዘገባ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም አቀፍ ሚዲያዎችም ጭምር ቀርቦ የተደመጠው፤ ልክ የዛሬ 10 ዓመት ከተከበረው የሚሌኒየም በዓላችን በኋላ ነው ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም ከዚያን ጊዜ በፊት ተጀምሮ የነበረው የሀገራችን ልማትና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ወደ በለጠ እምርታ እንዲሸጋገር ያደረገ አስገራሚ የመነቃቃት ስሜትን ፈጥሮልን ነው ያለፈው ያ በኢትዮጵያውያን የዘመን ቀመር መሰረት የዛሬ አስር ዓመት (2000 ዓ.ም) የተከበረው ደማቅ በዓል።

ይሁን እንጂ ግን፤ ያኔ መንግስት ያሳየውን ተነሳሽነት ተከትሎ ተፈጥሮ የነበረውን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵዊነትን ወደ ቀደመ ታሪካዊ ከፍታቸው ለመመለስ የመሻት መነቃቃት ግለቱን እንደጠበቀ ይቀጥል ዘንድ፤ መስራት የነበረብንን የቤት ስራ በአግባቡ ሰርተናል ማለት እንደማይቻል ነው ለኔ የሚሰማኝ። በዚያ ላይ ደግሞ ይህን የስር ነቀል ለውጥ እሳቤ እንደጦር ሲፈሩት የሚስተዋሉ የትምክህትና የጠበባብ ብሔርተኝነት ፖለቲካዊ አመለካከትን በማቀንቀን የሚታወቁ ፓርቲዎች እያሳደሩ ያለው አሉታዊ ትፅእኖ ሲታከልበት የኢትዮ-ሚሊኒየም 2000 ክብረ በዓላችንን ተከትሎ የተቀጣጠለው ሀገር አቀፍ የህዝብ መነቃቃት ቀስበቀስ ግለቱ እየቀነሰና እየተቀዛቀዘ መምጣቱ የሚያስገርም ጉዳይ አይሆንም። እናም መንግስት ራሱ አሁን ላይ ይፋ ያደረገው መርሐ ግብር ከዚህ አጠቃላይ እውነታ አኳያ ተገናዝቦ የተነደፈ ጠቃሚ አዲስ ዓመት አቀባበል ዕቅድ ነው ብየ አምናለሁ።

እንግዲያውስ መጪው ዘመን በእርግጥም የከፍታ እንዲሆን የሚል ርዕስ በሰጠሁት በዚህ መጣጥፌ ለማንሳት የፈለግኩትም ከላይ በመንደርደሪያዬ ለማመልከት የተሞከረውን መሰረተ ሃሳብ ጠቀሜታ ተቀብየ፤ ግን ደግሞ መጭውን ዘመን በእርግጥም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ከፍታ እንዲሆን ለማድረግ መርሐ ግብር ከመንደፍ ያለፈ ጥረት እንደሚጠበቅብንም እንደማምን የሚያትቱ ነጥቦችን ነው። ስለዚህ አሁን በቀጥታ ወደ ዋናው የጽሑፌ ማጠንጠኛ ነጥብ አልፍና በመጪው ዘመን የኢትዮጵያ የከፍታ ጉዞ ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፤ ብሎም ወደ ቀደመ ሀገራዊ ታላቅነታችን የመመለስ ህልማችን እውን እንዲሆን ማን ምን ዓይነት የቤት ሥራውን ሰርቶ መገኘት ይጠበቅበታል? ለሚለው ቁልፍ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ።

ስለዚህም በኔ እምነት፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለይም ከሚሊኒየም ሁለት ሺህ ክብረ በዓሏ ወዲህ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን እያገኘ በመጣ መልኩ የተያያዘችውን የህዳሴ ጉዞ ሲፈታተነው የሚስተዋለውን ተደጋጋሚ የቅልበሳ አደጋ እየጋበዘን ያለው ዋነኛ ምክንያት፤ በተለይም ስር ነቀል የሥርዓት ለውጥ ሂደቱን በፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከመፈረጅ የሚመነጭ ጽንፈኛ አቋምን የሙጥኝ የማለት አባዜ የተጠናወታቸው ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች የሚያራምዱትን ፍፁም ጨለምተኛ አስተሳሰብ፤ እየደፈቅን ተራማጁን አመለካከት የበላይነት ይዞ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ የሚጠበቅብንን ያህል የቤት ሥራ መስራት ስላልቻልን ነው የሚል አስተያየት አለኝ። ይህን የምልበት መሰረታዊ ምክንያትም ደግሞ፤ የዛሬዋ ኢትዮጵያ አንደ ሀገር የምትመራበትን ፌደራላዊ ስርዓት በቀለም አብዮት ካላስወገዱ ፈጽሞ እንቅልፍ ሊወስዳቸው እንደማይችል ከመናገር ቦዝነው የማያውቁት ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች፤ ከባህር ማዶ እስከ አገር ቤት በተዘረጋ ግልጽና ህቡዕ የዕክል ፈጠራ መረባቸው አማካኝነት፤ ምናልባትም ከመንግስት በተሻለ መልኩ ለአስተሳሰብ የበላይነት ትኩረት ሰጥተው ሲንቀሳቀሱ የሚስተዋሉበት አግባብ እንዳለ የሚካድ ጉዳይ አይደለምና ነው።

ለዚህ አስተያየቴ ማረጋገጫ የሚሆን ተጨባጭ ምሳሌ መጥቀስ ካለብኝም፤ በተለይ ከቀድሞው የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከአቶ መለስ ዜናዊ ህልፈተ ህይወት ወዲህ ባሉት ዓመታት ውስጥ፤ እየታተሙ የወጡትን የጽንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ድርሳናት (የአማርኛ መፅሐፍቶች) መመልከት ብቻ በቂ ይመስለኛል። ታዲያ በዚህን ያህል ዓለም አቀፋዊ የጽንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች የተጠና ቅንበር ታግዞ

የሚካሔድ አዲሱን የታሪክ ምዕራፍ አምርሮና አክርሮ የማጥላላት መጠነ ሰፊ ዘመቻ ተጧጡፎ በቀጠለበት ሁኔታ ውስጥ፤ የህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያዊነት መገለጫ ብሩህ መንፈስ ጎልቶ እንዲንፀባረቅ መሻት ተራ ምኞት ሆኖ እንዳይቀር መስጋት አይጠበቅብንምን ወገኖቼ? እኔ በግሌ ግን ይህ ዓይነቱን ፀረ የኢትዮጵያ ህዳሴ ጨለምተኛ አስተሳሰብ አሳምረን መስጋት የሚጠበቅብን ሆኖ ነው የሚሰማኝ።

አለበለዚያ ግን አጠቃላይ የስር ነቀል ለውጥ ሂደቱን "በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ" ቀልብሰው እነርሱ ወደ ስልጣን የሚወጡበትን አቋራጭ አጋጣሚ ለመፍጠር የሚፈልጉት የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ጽንፈኛ ፖለቲካዊ አመለካከትን አቀንቃኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ እንደ እስከ ዛሬው ሁሉ ከአገር ቤት እስከ ባህር ማዶ ድረስ በተዘረጋ የጥፋት ተልዕኮ ማስፈፀሚያ መረባቸው አማካኝነት ተመሳጥረው እያቀነባበሩ በሚያዛምቱት የበሬ ወለደ ዓይነት ተራ ውዥንብር ምክንያት የሚፈጠረውን ጨለምተኛ መንፈስ መጋፈጥ ግድ ሊሆንብን ነው። ያ ደግሞ መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ ይሆናል ሲል መንግስታችን ከወዲሁ ይፋ ያደረገው የብሩህ ተስፋ መርሐ ግብር ከተራ መልካም ምኞት ያለፈ ሆኖ እንዲገኝ ከማድረግ አኳያ ሲታይ ሊያሳድር የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለምና ጉዳዩን በደንብ ልናስብበት ይገባል እላለሁ።

እንዲያውም እውነቱን እንነጋገር ከተባለማ፤ ይህን የኢፌድሪ መንግስት ከነሐሴ 26 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ለምልዓተ ህዝቡ ይፋ ያደረገውን የ2010ን አዲስ ዓመት በተለየ ድምቀት ለመቀበል ያለመ መርሐ ግብር፤ ገና ከወዲሁ ለይስሙላ ብቻ የሚለፈፍና መሬት ላይ ወርዶ ሊታይ የሚችል ረብ ያለው ቁምነገር እንዲያስገኝ ታስቦበት ያልታቀደ እንደሆነ አድርገው በማጥላላት ዘመቻ፤ እንደተለመደው ሁሉ የመነቃቃት ጥረታችንን አዶልዱመው ለማስቀረት እየሞከሩ ያሉ ጽንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ጥቂት አይደሉም። በእርግጥ አዲሱን የ2010 ዓ.ም በተለየ መነቃቃት ለመቀበል ሲባል መንግስት ይፋ ያደረገውን መርሐ ግብር የሚደግፉና ምናልባትም ገዢው ፓርቲ ካካሔደው የጥልቅ ተሃድሶ መድረክ በኋላ ህዝቡ ይጠብቅ የነበረውን ትርጉም ያለው የእርምት እርምጃ የምናይበት ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ተፈጥሮም ጭምር ሀገሪቷ ከአሳሳቢ ችግሮቿ ትላቀቃለች ብለን ተስፋ እንድናደርግ የሚጋብዝ ሳይሆን እንደማይቀር ደፍረው ሲናገሩ የሚደመጡ አስተያየት ሰጪዎችም ጥቂት አይደሉም።

ስለዚህም እንደኔ እንደኔ፤ መጪው ዘመን በእርግጥም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ከፍታ እውን ሆኖ የሚስተዋልበት እንዲሆን፤ ወይም ደግሞ እንዳይሆን የማድረጉ ጉዳይ የሚወሰነው፤ በተለይም ስርነቀል የሥርዓት ለውጥ ጉዞውን ለማስቀጠልና ላለማስቀጠል ያለመ ትግል በሚያካሂዱት የፖለቲካ ኃይሎች ብርታትና ድክመት ነው ብሎ ማጠቃለል ተገቢ ይመስለኛል። በሌላ አነጋገር፤ ሀገር የመምራት ታሪካዊ ኃላፊነት የተጣለባቸው የፌደራሉ መንግስትና እንዲሁም የየክልላዊ መስተዳደሮቹ ባለድርሻ አካላት፤ ከላይ ለመጠቆም የተሞከረውን የጽንፈኛ ተቃዋሚዎች የማዶልዶም ተጽዕኖ ለመመከት የሚያስችላቸውን የፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ቁመና ተላብሰው እስካልተገኙ መርሐ ግብሩን ወደ ተጨባጭ ውጤት ተተርጉሞ ማየት የመቻላችን ጉዳይ አጠያያቂ ይሆናል ማለቴ ነው።

ስለሆነም መጪውን የ2010 ዓ.ም አዲስ ዓመት የምንቀበልበት የትግል መንፈስ ከዚህ አኳያ ተገናዝቦና የህዳሴ ጉዟችንን ለመቀልበስ ቆርጠው የተነሱት የጥፋት ኃይሎች በሚያሳድሩት ፈርጀ ብዙ ተጽዕኖ ልክ የተዘጋጀ ቁርጠኛ አመራር ሊኖረን እንደሚገባ የጋራ ግንዛቤ ተጨብጦበት እንዲገኝ መስራት ግድ ይላል። በተረፈ ግን አዲሱ የ2010 ዓ.ም በጀት ዓመት ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች የሰላም፤ የጤና፤ ብሎም የእድገትና የብልጽግና ብሩህ ዘመን ይሆንላቸው ዘንድ ልባዊ ምኞቴን እየገለጽኩኝ፤ እነሆ የዛሬውን ሐተታዬን እዚህ ላይ አበቃሁ።